የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፳፫
አዲስ አበባ-ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 23
ADDIS ABABA- 27th January , 2004

## ማውጫ

**አዋጅ ቁጥር ፫፻፹፰/፲፱፻፺፮ዓ.ም**

ከኔዘርላንድ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ጋር ኢንቨስትመ ንትን ለማበረታታትና ጥበቃ ለመስጠት የተደረገውን ስም ምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ...............ገጽ ፪ሺ፭፻፵፮

## CONTENTS

**Proclamation No. 388/2004**

The Treaty on Encouragement and Reciprocal Protection of Investment with the Kingdom of Netherlands Ratification Proclamation. ............ Page 2546

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፹፰/፲፱፻፺፮

### ከኔዘርላንድ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ጥበቃ ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በኔዘርላንድ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ጥበቃ ለመስጠት የሚያስችል ስምምነት ግንቦት ፰ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፤

ስምምነቱ ሥራ ላይ የሚውለው በተዋዋይ ሀገሮች ሕጎች መሠረት ስምምነቱ መጽደቁን የሚያረጋግጡ ሰነዶች በዲፕሎማቲክ አካላት አማካኝነት ልውውጥ ከተደረገ በኋላ እንደሆነ በስምምነቱ በመገለፁ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል::

## PROCLAMATION NO.388/2004.

### A Proclamation to Ratify the Treaty on Encouragement and Reciprocal Protection of Investment between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Kingdom of the Netherlands

**WHEREAS,** the Treaty on Encouragement and Reciprocal Protection of Investment between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Kingdom of the Netherlands is signed in Addis Ababa, May 16,2003;

**WHEREAS,** it is stipulated in the Treaty that it shall enter into force on the date of exchange of instruments of ratification through diplomatic channel;

**WHEREAS,** the House of the People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has rarified the said Treaty at its session held on 27th day of January, 2004

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Article (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ከኔዘርላንድ ንጉሡ ነገሥት መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ጥበቃ ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፫፻፹፰/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## ፪. ስምምነቱ ስለመጽደቁ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኔዘርላንድ ንጉሡ ነገሥት መንግሥታት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ጥበቃ ለመስጠት በአዲስ አበባ ከተማ፣ ግንቦት ፰ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም የተፈረመው ስምምነት ፀድቋል::

## ፫. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኃላፊነት

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ስምምነቱን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል::

## ፬/ አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "The Treaty on Encouragement and Reciprocal Protection of Investment with the Kingdom of the Netherlands Ratification Proclamation No.388/2004."

## 2. Ratification of the Treaty

The Treaty on Encouragement and Reciprocal Protection of Investment signed in Addis Ababa on May 16, 2003 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Kingdome of the Netherlands is ratified.

## 3. Responsibility of the Ethiopian Investment Commission

The Ethiopian Investment Commission is hereby empowered to implement this Treaty.

## 4. Effective Date

The Proclamation shall enter into force as of 27th day of January, 2004.

**Done at Addis Ababa, the 27th day of January, 2004**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**